# ሁሉን አቀፍ የምክክር ጉባኤ ከ ጃንዋሪ 14 እስከ 15፤ በዋሽንግተን ዲሲ ይካሄዳል!

ቀን፤ ህዳር 28፣ 2008        ዲሴምበር 7፣ 2016

በሀገራችን ውስጥ የሚታየውን የግፍ አገዛዝ አስወግዶ በኢትዮጵያ አንድነት ስር የስርአት ለውጥ ለማምጣት የሚችል ሰፋ ያለ የተቃዋሚዎች ትብብር መፍጠር ጊዜ የማይሰጥ አንገብጋቢ አገር አድን ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበን፤ ለተግባራዊነቱ በጋራ ስንቀሳቀስ ቆይተናል። ሂደቱንም በሚመለከት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማሳየት በተለያዩ የዜና አውታሮቻና መገናኛዎች ለቀረቡልን ቃለ መጠይቆች ማብራሪያ በመስጠት ላይ እንገኛለን። ለበለጠ መረጃ  በሴፕቴምበር 07 ፣ 2016 እና በኦክቶበር 13/2016 ያወጣናቸውን የጋራ መግለጫዎችና የሰጠናቸውን ማብራሪያዎች በጥቂቱ ለመመልከት የሚከተሉትን ሊንኮች ይጫኑ፤

[የሴፕቴምበር 7 መግለጫ](#)   [የኦክቶበር 13 መግለጫ](#)   [SBS ራድዮ ቃለ-ምልልስ](#)   [አማራ ድምጽ ራድዮ](#)

ከዚህ በተጨማሪም ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የሁለትዮሽ ውይይቶች በማድረግና የግብዣ ደብዳቤዎችን በመላክ ሂደቱን በጋራ በማካሄድ ጉባኤውን እንድናዘጋጅ ወይም በጉባኤው እንዲሳተፉ ጥረት ስናደርግ ቆይተናል፤ የተወሰኑትም እንደሚሳተፉ በፅሁፍ አረጋግጠዋል። በዚህ አጋጣሚ ያደረግነውን አገራዊ ጥሪ ወቅታዊነት በመገንዘብ፤ ለመሳተፍ ፍቃደኛ መሆናቸውን በደብዳቤ ምላሽ ለላኩልን ድርጅቶች በሙሉ ምስጋናችንን ማቅረብ እንወዳለን።

ከጃንዋሪ 14 እስከ 15፤ 2017 የሚካሄደውን ጉባኤ ሂደት የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለህዝቡ በቀጥታ ስርጭት እንዲተላለፍ ይደረጋል። የጉባኤው ፕሮግራም ዝርዝርና ተያያዥ ጉዳዮችን በተከታታይ እንገልጻለን። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ድርጅት ከታች ከተገለፁት አድራሻዎች በአንዱ ሊያገኙን ይችላሉ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ያሸንፋል!

**የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋር ትግል ሸንጎ** (SHENGO)
**የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት** (ENTC)
**የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ** (EYNM)

**ለበለጠ መረጃ፤**   ENTC contact@etntc.org   EYNM ethiorevolution@gmail.com   SHENGO **shengo.derbiaber@gmail.com**